ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

ቀን

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በታኅሣሥ 11 2010 ዓም የተላለፈ ሀተታ

# ዕባብ ቆዳውን ቢሽለቅቅ ፤ መርዛማነቱን አይለቅቅ !

ሁልጊዜ በየዐመቱ በሀገራችን የበልግ ወራት ሲመጣ፤ ዕባብ ቆዳውን ሽምቅቆ እያስወገደ በአዲስ ቆዳ ይተከዋል ። መርዙን ግን አጭቆ በማስቀረት፤ ሌላውን ለመንደፍ ይጠቀምበታል ።በአካባቢው የሚያገኛቸውን ተንቀሳቃሽ ነፍሳት፤ አዕዋፍን ጭምር በመርዙ እየነደፈ ይፈጃቸዋል ።ሰውን ካገኘም መንደፉን አይተውም " **ሰው እራስክን የቀጠቅጥሃል፤ አንተም ሸኮናውን ( ዕግሩን ) ትነድፍዋለኽ !** " በተባለው ትዕዛዝ መሠረት ይፈፀማል ።

አምባገነን አገዛዝና ሕዝብ ፤ ዕሳትና ገለባ፤ አጥፊና ጠፊ፤ ነዳፊና ተነዳፊ በመሆናቸው፤ አምባገነኖች መርዛቸውን ሲተፉ ፤ ሕዝቡም ከመርዙ ለመከላከል ሲል እያመፀ ጭንቅላታቸውን ይቀጠቅጣቸዋል ። በመነደፍና በመቅጥቀጥ መካከል ያለው ትንቅንቅ ፤ ተናዳፊውን መርዘኛ ዕባብ ላንዴና ለመጨረሻው እስኪሲያስወግዱት ድረስ ዘልቆ ይሄዳል ። አጥፊና ጠፊ በሠላም አብሮ መኖር አይችሉም። ዕሣትና ገለባ በመሆናቸው፤ አዝመራውን ለማዳን በግድ ዕሣትኑ መጥፋት ግድ ይሆናል ።ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማዳን፤ ተናዳፊውን መርዘኛ ዕባብ መስወገድ የመጀመሪያ ደረጃ ቅድሚያ መሆን አለበት ።

በዚህ ሃሳብ ሁሉም ያምንበታል ። ጥያቄው ግን፤ ወያኔ እንዴት ይወገድ ? የሚለው ነው። መልሱን አብረን እንጠይቅ የሚል ፤ የባተሌ አነገገርና ኃላፊነት የጎደለው ኃሳብ ወርውሮ ማለፍ አንሻም ። ቢሆንም፤ሁሉም ድርጅትና ሁሉም ዜጋ አበክሮ እንዲያስብበት ደጋግመን ማሳሰባችንን እንቀጥላለን ።

ሰሞኑን የወያኔ ቡድን፤ ረዥም ስብሰባ ሲያካሂድ ቆይቶ፤ አሮጌ ቆዳውን በመሽልቀቅ አዳዲስ መርዘኛ ግለሰቦቹን መርጦ ለአጥፊ ሥልጣን/ተልዕኮ ሰይሞ ተበትኗል ። ከማረጣቸው ዘጥኝ መርዘኛ ገለቦች መካከል፤ ስድስቱ አባላት የዐደዋ ተወልጆች ናቸው። በተናዳፊነታቸው፤ የሚደንቁ እንደሆኑም ይነገራላቸዋል ። ወያኔ ፤ የቆየውን ትቢያ እያራገፈ፤ አቧራውን ጠራርጎ፤ በአስመሳይ ለውጥ ተሸፋፍኖ ሕዝብ ለማታለል ሞክሯል። ሙከራው ሁሉ ግን አሸዋ በልቶት ቀርቷል። ይኸ ስብሰባ የዐደዋን ሥርወ- አጋዛዝ ተክሏል። አዲሶቹን ዘጠኝ አባላት በሦስት የምድብ ቦታዎች ተደልድለዋል፡ እነርሱም፡-

**1ኛ.** ደብረ ጽዮን ግብረሥላሴ፤ አዲስ ዐለም ባሌማና ኪርያ ኢብራሂም በትግራይ ክልል ፤

**2ኛ.** ዐለም ግብረዋኅድና ፤ ጌታቸው ረዳ በወያኔ ( ህወሐት) ጽ/ቤት

**3ኛ.** ፍትለወቅ ግብረ እግዚአብሄር ፤ አስመላሽ ወልደ ሥላሴ፤ አብረሃም ተከስተና ጌታቸው አሰፋ፤ ፌዴራል መዋቅር በሚሉት አዲስ አበባ ተመድበዋል ።

የወያኔ ካርታ ብወዛ፤ አንድ ጠረጴዛ የቁማር ጨዋታ ከሚያሳየው ክርክር አልፎ ፤በሀገራችን ስር የሰደደ ችግር ላይ የሚያመጣው ልውጥ አይኖርም ። ይኸ አሰልች የቁማር ካርታ ብወዛ፤ በተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ላይ አንዳችም ተፅዕኖ አያሳድርም። የሕዝቡንም የትግል አቅጣጫም ሊያስለውጥ የሚችልበት ዐቅም አይኖረውም። ለዚኽ ማስረጃ የሚሆነውም፤ ወያኔ ስብሰባውን ጨራስኩ ካለ በኋላ ማግስት በይበልጥ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እየተፋፋመ መሄዱ ነው።

በተለያዩ ክፍለ ሀገራት በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የሚማሩ ተማሪዎች አማጻቸውን በተጋድሎ ቀጥለዋል። በርካታ ተማሪዎችና ሌሎች አማፅያን የሀገሪቱ ወጣቶች መሥዋዕት የሚጠይቀውን አመፅ እያፋፋሙት በመሄድ ላይ ናቸው። የወጣቶቹ ተጋድሎ ፤ዘርና ቋንቋን ከመ-ጤፍ ሳይቆጥር፤ በዘለዓላማዊቷ ኢትዮጵያ ላይ መሠረቱን ጥሎ የሚቀሳቀስ መሆኑ ቢታወቅም፤ ነፍስ

ገዳዩ የወያኔ  ዐጋአዚ ጦር ግን የሚፈጽመው ወንጀል ዘር እየለየ በኦራሞና በአማራ ተመሪዎች ላይ እንደሆነ በአደባባይ የሚታይ ሃቅ ነው።

በወልደያ፤ በኮምበልቻ፤ በባህር ዳር፤ በጎንደር፤ በደብረታቦር፤  በጅማ፤ በደብረ ማርቆስ፤ በሐረር ጨለንቆ፤ ተማሪዎች የሚፈሥሠው የንፁሃኑ የኢትዮጵያውያን ደም  ፤ በሚያሳዝን ሁኔታ ቀጥሏል። የሕዝቡ አመፅ ፤ እየቀጠለ  እስከሄደ  ድረስም የንፁሃኑ ደም  መፍሰሱ ፤ በከፋ መልኩ መቀጠሉ አይቀርም ። ሕጋዊ የሕዝብ ጥያቄ አስካልተመለሰ ደርስ ፤ ሕዝባዊው አመፅ አይገታም።  ትግሉም ግብን እስካልመታ ደረስ አይቆምም ።

 የወያኔ ጦር ሁሉንም ጨርሶ አይጨርስም።ከታሪክ ሊማር ይገባዋል ። ከሕዝብ ማኅፀን የወጣ በመሆኑ ፤አንድ ቀን ዐለቆቹን ተቃውሞ፤ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆሙ አይቀሪም ። በዐለቆቹ ላይ አፈሙዙን ማዞሩ የማይቀር የታሪክ ሃቅ ነው። ያን ጊዜ፤ አኩሪና አስመስጋኝ ታሪክ ይሰራል ። ያስቀየመውንም ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቃል ።  ሕዝቡም ይቅርታውን አይነፍገውም ። ጊዜው ሳይመሽ ፤ ወታደሩ፤ አፈሙዙን  ማዞሩ የሚገባው በሕዝቡ ላይ ሳይሆን ፤ በወያኔ መሪዎች ላይ መሆን እንዳለበት ሊረዳው ይገባል ። ይኽንን ማድረግ ከቻለ፤ ሀገሪቱን ካንዣበባት የደም ጎርፍ ሊያድናት ይችላል።

 የወያኔ አመራር፤ ከትግራይ- አቅፍ ወደ  ዐደዋ ማጀት ቢሸጋሸግም፤ የሀገራችንን ነበራዊ ሁኔታ ሊለውጥ የሚችልበት ቁመና አይኖረውም።  እንስካሁን  ድረስ፤ በጎሣና በቋንቋ ሲሽመደመድ የቆየው ዘርኛው ቡድን ፤ እንደ አይድራ ( ) ተባይ እርስ-በራሱ እያተብላላ ቆይቶ አሁን ሕልፈተ-ህይወቱ መቃረቡን ሲረዳ ፤ የመጨረሻ እስትንፋሱን ለማቆየት ሲል፤ የውስጥ ጥግና ለውጥ በማድረግ እራሱን ያታልላል ፡፡ ራስን የማታለል  ችሎታ ያለው ደግሞ ሌላውንም የማታለል ክኅሎት አለኝ ብሎ ራሱ በድጋሜ ያታልላል። ሌላውን አታልያለሁ ብሎ ካመነ ደግሞ፤  ሁሉንም የመናቅ ድፍረት አለኝ ብሎ ያምናል።   የወያኔ መሪዎች ራስን ብቻ  የማታልል ክህሎት አላቸው። ሌላውን ለማታለል ግን አልቻሉበትም። በተለይም ደግሞ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ !

 ሌላውን የመናቅ ድፍረታቸው ግን ፤ ከመላው የሀገሪቱ ሕዝብ አልፎ ተርፎ፤ እታገልለታለሁ የሚሉትን  የትግራይን ሕዝብ ጭምር ደፍረውታል ። ከሌሎቹ ስድስት  የትግራይ   አውራጃዎች  ተጠራቅሞ፤ የታገለውን አባላት እያስወገደ በአድዋ ተወላጆች  እጅ ብቻ ሥልጣኑን አከማችቶ ብቅ ብሏል።  ከስድቱ የትግራይ አውራጃዎች የመጡትን አባላት ሊያምናቸው አልቻለም  ። ከእነርሱ ጋር በተፈጠረው መጠራጠርና  የእርስ  በእርስ ፍትጊያ  ምክንያት፤  የወያኔ ድርጅት ጃርት የበላው ዱባ ከሆነ ቆይቷል። የዚኽ ሁሉ ምክንያት ደግሞ፤  የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እያየለ መምጣቱ ነው። ይኽም በበኩሉ ፤ በወያኔ  ሰፈር፤ ፍርሃትን፤ ሽብርን መቅበዝበዝንና መቅበጥበጥን አስከትሏል ።

 ወያኔዎቹ ጨካኙ ናቸው። ጭካኔ የሚፈጠረው ደግሞ ከፍረሃት ነው። ከፍርሃታቸው የተነሳ፤ ሁሉንም ጠልተው ሁሉንም ይፈራሉ ። ጭካኔንና ፍርሃትን የወርሱት ደግሞ ከደርግ ነው። የደርግንም ፈለግ ተከትለው መጥፋታቸው አይቀርም ።

ይኽ ሁኔታ በወያኔ አመራር ውስጥ ያልተጠበቀ ቀውስ ዱብ እዳ ስለሆነበት፤   እንደ ቆሰለ ዐውሬ የተቅበዘበዘ ባኅርይ አስከተለበት። ጅራቱን ቆልፎ ወደ አድዋ  ህድሞ( ካብ ) ለመግባት ተገደደ ። የሌሎች አውራጃዎች ተወላጆችንን፤ እንድ አሮጌ ቁና ወርውሮ  ፤ያዋጣኛል ብሎ ያመነበትን አውራጃዊ ምሽጉን አጠነከረ። እየጠበበ  እየጠበበ ፤ ወርዶ ወርዶ ፤ አደዋ ወይ ሞት! ከሚል ማሳረጊያ ደረሰ። የዐደዋ ተወላጅ ባልሆኑት ላይ ንቀትን አሳይቶ አስከፋቸው። " **ላይክስ  አይበድለም !** " ሆነና፤  አዲስና ሌላ የተቃዋሚ ግንባር ተፈጠረ ማለት የሚያስችል ሁኔታ ተከሰተ ።

 ከዐደዋ ውጭ ያለውና ቀሪው የትግራይ ክፍለ ሀገር ሕዝብም ሆነ ታጋዩ ክፍል፤ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆኖ ተባብሮ እንደሚታገልና ሀገሩንም ከወያኔ አምባገነን አገዛዝ እንደሚያላቅቃት ሁኔታዎቹ ተመቻችተውለታል  ።  ምን ጊዜም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ ፤ የቆየ ታሪኩም ሆነ መፃዒ ዕድሉ፤ ከወገኑ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሳሰረ መሆኑን አብክሮ ይረዳል ። የወያኔ እንደ  ዕሥሥት መለዋወጥም ሆነ የአደዋ ሥርወ- አጋዛዝ  አመራሮችን መሰየም፤ ይኽንን  ሀቃ ሊለውጠው አይችልም።

እስከአሁን ደረስ፤ የተቃዋሚ ክፍሉን እነየናቀ፤ በማን- አለብኝ፤ ያሻውን ሲፈፅም ቆይቶ አሁን ደግሞ የትግራይን ሕዝብ መናቅ ጀምሯል። መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ሊንቅ አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የማይናቅ ሕዝብ መሆኑንም ሳይረዳ አልቀረም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ በእዮብ ትዕግስት የተጎናፀፈ መሆኑ ቢታወቅም ፤ የትዕግስቱ ፅዋ ሞልቶ ሲገነፍል ግን ፤ ሕዝባችን ፤ ጥላቶቹን ሁሉ እንደ ዕሳተ-ገሞራ ፤ ዶግ ዐመድ የማድረግ ችሎታ እንዳለው መታወቅ ነበረበት። ወያኔዎች ግን ይኽንን ገና አልተረዱትም ።

በታሪክም ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የናቁ፤ የተተናኮሉ፤ የተዳፈሩና የተቅለበለቡ ሁሉ፤ አንድ -በአንድ ድራሻቸው ጠፍቶ ቀርቷል። የዐደዋው ቡድን መጨረሻው ከዚኽ የተለየ ሊሆን አይችልም።

አሁን በስፋት፤ ብኅብረትና በፅናት የቀጠለው ሕዝባዊ አመፅ ተጠናክሮ ይቀጥላል ። የማይገታ ፤ የማይበገርና የማይፈታ ዐመፅ ነው ። የሀገሪቱን ሉዕዋላዊነት ብቻ ሳይሆን፤ የዜጎቿንም አንደነት እንደገና አጠናክሮ የሚያረጋ ግጥበትንም ዘመን አብሳሪ ሆኖ ይቀጥላል ፡፡ ምናልባት በአሁኑ ወቅት፤ሕዝባዊው ዐመፁ፤ ማዕከላዊነት የጎደለውና ሁነኛም መሪ የለውም ተብሎ ሊገመት ይችል ይሆን ይሆናል ። ይኽ ግን ከግመት የማያልፍ ግምት ሆኖ ይቀራል ።

በታሪኩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን መሪ ማውጣቱ ባይዘነጋም፤ መሪዎቹ ግን የሕዝቡን ዕምነትና ቃል ኪዳን ጠብቀውልኝ ነበር ለማለት አልታደለም ። እያመናቸው ይከዱታል። ተስፋውን አቀጭጨውበታል። አሁንም ዕውነተኛ መሪዎቹን ፈላጋ ላይ ይገኛል ። አምባገነን ማሪዎችን ታግሎ የመጣሉን ያኅል፤ ሁነኛ ታማኝ መሪዎችን መምረጥ ግን አልቻልም። አልታደለም። የባሰውን ሸኝቶ፤ በተሻለ መተካት አልተሳካለትም። የሀገራችን ጉዳይ ቢይዙት ቢጨብጡት፤ ቢያነሱ ቢጥሉት- ቢጨብጥት ፤ እንደ ሸንበራ ቂጣ ቢያገላብጡት ፍንክች ሊልልን አልቻለም። ለአለፉት አምሳ ( 50 ) ዐመታት ፤ ከንጉሣዊ አገዛዝ ፤ እስከ ወታደርዊ አባገነን አገዛዝ እና እስከ ዘረኛ ጠባብ ጎሣ አራማጅ ብሄረተኛ አገዛዝ ተፈረረቁበት። ግን ዕጣ-ፋንታው አልተሻለለትም ። ይኽን ሀቅ ማንም አይከራከርበትም ።

ቢሆንም፤ ተተኪው ምን ይሁን ? ማን ይምጣ ? እንዴት ይምጣ ? ከዚኽ የታሪክ ሰቆቃ ተንስተን እንዴት ወደ ተሻለ ጎዳና መራመድ አቃተን ? የተሻለ ሥረዓተ- መንግሥት ለመመሥረት ምሥጥሩ ለምን ተሰውረብን ? ሌሎች ሀገራት ያገኙትን ብልሃት ለምን ለኛ ተሰወረብን ? እረ ለመሆኑ፤ የተሻለ ሥር ዓተ-መንግሥት እናመጣልን ብለው የሚታገሉ ድርጅቶች፤ እርስ በእርሳቸው በዕርግጥ ይተዋወቃሉ ? የኢትዮጵያንስ ሕዝብ፤ ማወቅ የሚገባቸውን ያኅል ያውቁታል ? የነኝኅንና የተመሳሳይ ጥያቄዎች መልሶች አሉን ለማለት አንቃጣም ። ያላቸው ካሉ፤ ለመማር ዝግጁ ነን ። ነገር ግን፤ ጥያቄዎቹ ሁሉ አግባብነት ባላቸው መልሶች ከተጠናከሩ ፤ ሁሉንም ወደሚያስማሙ መድረክ ሊያመሩ ይችሉ ይሆናል ።

ኢትዮጵያውያን ተስማምተው በኅብረት ለሀገራቸው መፍተሄ ካላስገኙ ፤ የወያኔዎች ትያትር ተውኔት ተመልካች ከመሆን አያልፉም። ወያኔ ግን፤ ከትግራይ ክፍለ ሀገር፤ ወደ አድዋ ኽድሞ ቢመሽግ የሀግራችንን ችግር ለመፍታት፤ ራዕይም ሆነ ፍልጎት፤ ቆመና ሆነ ችሎታ የለውም ። የሀገራችንን ስር የሰደደ ችግር መፍታት የሚችለው ራሱ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው ። አራት ነጥብ !

ያም ስለተባለ ግን ፤የሀገራችንን ጉዳይ በአራት ነጥብ አስቀምጦ መገላገል ይከብደናል።አንሞከረውም! ቢሆንም፤ የሚከተሉትን ግንዛቤዎች ማስተላለፍ እንፈልግለን ፡---

**1ኛ.** የወያኔዎቹ የቦታ መቀያየር የሕዝባችን ጉዳይ አይደለም። በራሳቸው አጀንዳ እራሳቸው ይደንከሩበት።

**2ኛ.** በወያኔዎቹ ቲያትር የኢትዮጵያ ሕዝብ የትኩረት አቅጣጫውን ሊስት አይችልም ፤ አይገባውምም።

**3ኛ.** ወያኔዎቹ ፤ ከዘር ፖለቲካ ውጭ ሌላ ህይወት የላቸውም ። ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚገኘው ከዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ ጋር ብቻ ነው። ይኽንም ዕውነታ፤ የትግራይ ሕዝብ በሚጋባ ያውቀዋል። ይረዳዋል።

**4ኛ. " አንበሳና ነብር ሲጣሉ፤ ግልገሏን ንስር እንደወሰዳት "** ሁሉ ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳችን ስንፏከት፤ ጠላቶቻችን ሀገራችንን እያጠፏት መሆናቸውን መረዳት እጅግ አስፍላጊ ነው። ልብ ላለው ዜጋ፤ የ1966 ቱ ዓ/ም መራራ ተመክሮ፤ ብዙ ትምህርት ያስተምረዋል ።

**5ኛ** አሁንም ፤ እንደትላንቱ፤ የሕዝቡን ትግል ነጥቀው ለራሳቸው ሥልጣን መቆናጠጫ ለማድረግ አስፍስፈው የሚጠባበቁ እንዳሉ መዘናጋት አይገባም ። **" ወያኔ ብቻ ይወገድ እንጅ፤ የፈለገው ይምጣ "** የሚለው ገልቱ አስተሳሰብ፤ ብልኅነት አይደለም ። ደርግ ሄዶ ወያኔ መተካቱን የሚዘነጋ ኢትዮጵያዊ አለ ብለን አናስብም ።

**6ኛ.** የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አመፅ በሁለንተናዊ ረገድ፤ ማገዝ የሁሉም ግዴታ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !